# ቅንጅቶቹ ኢትዮጵያውያን

ከይድነቅ (ኖርዌ)
yfyidnek67@gmail.com

የሰሜኑ ጫፍ የክረምቱ ጨለማ ወቅቱን ለበጋዋ ብርሃንና ፀዳል ሊለቅ ጓዙን ጨርቁን ጠቅልሎ ለከርሞ ያድርሰን የሚል ይመስላል። ጸደይ ላይ ብዙም አይበርድም። ደንደን ያለ ሰውነት ያለው ስስ የበጋውን ሸማ ቢያደርግ እንኳን ቅዝቃዜው ይህን ያህል ዘልቆ አይገባም። እኔ እንደተለመደው ብቻዬን ስንጎራደድ ድንገት ባቡር ጣብያው መናኸርያ እግር ጣለኝ።

ጓደኛዬ በሙሉ ልብስ እስከነከረባቱ አሸብርቆ ከባቡር ሲወርድ ድንገት ዓይን ለዓይን ገጠምን። አንገቱን ቀና አድርጎ ወድያና ወዲህ እየቃኘ ሲንጎማለል የፍቅር እስከመቃብሩ ፊታውራሪ መሸሻ ትዝ አሉኝ። አጠገቤ እስኪደርስ ዝም ብዬ አስተውለው ጀመር። "ምን እያደረክ ነው? ሲል ጠየቀኝ። በእርግጥ ፈረስ ላይ አይደለም እንጂ ድምጹ ቁጭ ፊታውራሪ መሸሻን። እኔ ገና ጉስቁል እንዳልኩኝ ነኝ። የብርዱ ሸማዬን ወፍራሟን ጃኬቴን ገና አላወለኩኝም። "አይ - ዝም ብዬ ዞር ዞር እያልኩኝ ነው። ምን መሄጃ አለኝ ብለህ ነው" - አልኩት። "አዎ አንተ ዙር፣ ዝም ብለህ ዙር - አለኝ" እንደፊታውራሪ መሸሻ ወደ ሌላ አቅጣጫ እያማተረ። "ና እስቲ!" - ብሎኝ ማዶ ካለው ቡና ቤት ድረስ እንድከተለው በአገጩ ጠቁሞኝ ከፊት ቀደመ። "ጓደኛዬ ዛሬ ምን አገኘ?" እያልኩኝ የባጥ የቆጡን አወርድ ጀመር።

ቡና ቤቱ ደርሰን ወንበር ስበን ተቀመጥን። ሊታዘዘን የመጣው ወጣት በፈገግታ ሰላምታ ሰጠን። "ሁለት ቢራ አምጣልን" – አለው ጓደኛዬ በቀጭን ትዕዛዝ። "ቦታ ልትቀይሩ ትችላላችሁ። ይህ ቦታ ምግብ ጭምር ለሚያዙት የተዘጋጀ ነው" - "ይቅርታ" - አለ በትህትና አሳላፊው። ፈረንጆች ትህትና ያውቁበታል። ጓደኛዬ ፊታውራሪ መሸሻን አክሎ ስለነበር ቦታውን ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም። "የሚበላ ለሱ አምጣለት" አለው። በእርግጥ እኔም አልበላሁም ነበርና ከቢራው በፊት ምግብ ስለታዘዘልኝ በልቤ ደስ ተሰኘሁ። አስተናጋጁ ሜኒውን አቀረበልኝ። የምፈልገውን መረጥኩኝ። ጓደኛዬ አሁንም ሌላ ቦታ ነው ዓይኑ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ቢራችን ቀድሞ መጣ። እንደቀድሞው ብርጭቋችንን ለማጋጨት ስጠብቅ ጓደኛዬ ቀድሞ ተጎነጬ። እንደገናም ተጎነጬ።

"ለመሆኑ ቅንጅት ምን ማለት እንደሆን ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀኝ። አሁንም ማዶ ማዶ እየተመለከተ። "እንዴ ቅንጅትን ማን ያጣል?" አልኩት። "ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲን ማን ይረሳል?" አልኩ ቀጠል አድርጌ። ቢራውን ጎንጨት ጎንጨት እየደረገ ግማሽ አደረሰው። "ጠጣ እንጂ" - አለኝ። ማዝገሜን አስተውሎ። ሰለ ቅንጅት እያወራሁ ሳለ የታዘዘው ምግብ መጣ። ሌላ ቢራ ታዘዘ። ርቦኝ ነበር ቶሎ ቶሎ በላሁ። ቢራዬን ጎንጨት ጎንጨት አደረኩኝ። ጉድ እኮ ነው ቢራዋ እኔም እንደፊታውራሪ አሰጌ ቀና ቀና ልታደርገኝ ነው መሰለኝ።

ብቻ ሁለተኛዋ ቢራ ሁለታችንንም ውስጣችንን ማቀዝቀ ጀመረች። የፊታውራሪ መሸሻ ውቃቢ ከጓደኛዬ ትከሻ ላይ ግፍፍ ሲል አስተውላለሁ። እኔም እንኳንስ ፊታውራሪ አሰጌን ይቅርና ጓንዴ ተሸካሚያቸውን መሆን አልቻልኩም። ቢራዋ ወደ ማንነታችን መለሰችን። ሁለታችንም ስደተኖች ነን። ስደት አኮስሶ አቀዝቅዞ ካጋደመን አመታት አልፈዋል። በረዶው እየተፈራረቀብን፣ ጭለማው እያዳፋን ፖለቲካው እያዋዠቀን ፈሪዎች፣ ቶሎ ብስጩዎች፣ ሆደባሻዎችና ጎስቋሎች ካደረገን ቆይቷል።

"ቅንጅት ስልህ እተጠራሁበት ግብዣ ላይ ያየሁትን ኢትዮጵያዊውን ቅንጅት ማለቴ ነው" አለ ጓደኛዬ። ሳቅ ሳቅ ማለት ጀመረ። እፊቱ ላይም ግራሞት ይታያል። "እየውልህ አድምጠኝ" አለኝ ከረባቱን እያላላ።

"ሚስትየዋ በማህበራዊ ጉዳይ ላይ ከዘመድ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ አይርቁም። ባልየው ደግሞ በአንድ ታዋቂ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ አንቱ የተባሉ ሰው ናቸው። ተመካክረው ሲወስኑ፣ ተጠባብቀው ሲራመዱ ላያቸው ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው። ባልና ሚስቱ ተቀናጅተው ሰውንም ማቀናጀት፣ ማሰባሰብ ያውቁበታል። ይኸውልህ በልጃቸው የእምነት ማጽናት በዓል ላይ ጠርተውኝ እዚያ ውዬ ነው የመጣሁት" – አለኝ። "እነማን ናቸው እኔ

አውቃቸዋለሁኝ እንዴ? አልኩት። "አታውቃቸውም" ። "ይልቅስ ስማኝ" ብሎ ንግግሩን ቀጠለ።

"ድግሱ በአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ነበር የታደመው። ያልተጠራ፣ ተጠርቶ ያልመጣ ሰው አልነበረም። ሁሉም አጊጦ አሸብርቆ በዓሉን አድምቆታል። በዓሉ የመደብ፣ የኀጥና ፖለቲካዊ ልዩነቶች አይንጸባረቁበትም። በዚህ ሀገር ላይ የጎላ የደሃና ኃብታም ልዩነት ባይታይም እንኳን ሥራ ያለውም ሥራ የሌለውም መምጣቱ መደባዊ ልዩነቱን ሲያስቀር፣ ከሁሉም ብሔር የተውጣጡ ኢትዮጵያውያን ባንድ ገበታ ላይ መቅረባቸው ደግሞ የዘር ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል። በግብዣው ላይ ኤርትራውያኖችም መገኘታቸው ደስ ሲያሰኝ፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች በሕብረት መቀመጣቸው ደግሞ የመቻቻሉን ምስጢር ከፍ አድርጎታል።

እዚያ ማዶ ስመለከት መንዜው ለጉራጌው ጓደኛው በልዩ ሙያ የተዘጋጀውን ዶሮ ወጥ ሲያጎርሰው ጉራጌውም በተራው ያንን እጅ የሚያስቀረጥመውን ክትፎ በጣቶቹ ይዞ "በሞቴ" ብሎ ሲነሳ የተመለከትኩትን ለሠዓሊ ብተወው ይሻላል። እታች ማዶ ደግሞ ትግሬው ጉብልና ቆንጆዋ ኦሮሞዋ ሸጋ ሲሳሳቁ አጠገባቸው የተቀመጡት ሲዳማው፣ ሃደሬው፣ ጎጃሜው፣ ወሎዬውና ሌሎችም ስለ አዲሱ ሥራ ቦታቸው ያወጋሉ። አጠገቤ የተቀመጠው አንድ ጉብል ኤርትራዊ ደማሟን ኢትዮጵያዊ ኮረዳ ያሽኮረምማል። እንደው ግርም ቢለኝ ድንገት ወደ ኋላዬ ስዞር ያለፈው ሰሞን በአባይ ቦንድ ሽያጭ መዘዝ ቡጢ የተሰነዛዘሩ ሁለት ፖለቲከኞች የደራ ጨዋታቸውን በጠጁ ያሚሻሉ። እረ ስንቱ፣ እታችኛው ጠርዝ ላይ ላይ ደግሞ አንተ ወያኔ ነህ፣ ቅንጅት ነህ፣ ኢሕአፓ ነህ፣ ኦነግ ነህ፣ እየተባባሉ ሲናቆሩና ሲገለማመጡ የነበሩት ሁሉ ባንድ ጣራ ሥር ካንድ ማዕድ ሲቆርሱና ሲገባበዙ ይታያሉ።

በርካታ ኢትዮጵያዊያን በምግቡ ጣዕም ተወድሰው በጠጁ ጣዕም ታውደው ባለቤቶቹ ባዘጋጁላቸው ድንቅ ማህበራዊ አጋጣሚ መደሰታቸው ከፊታቸው ላይ ይነበባል። አንዳንዶቹ ከባህል ዘፈኑ የተነሳ የሃገር ሽታን፣ የወገን ናፍቆት ቀስቅሷቸው ትከሻቸውን ሲነቀንቁ ይታያሉ። "ኢትዮጵያ" – "ኢትዮጵያ" - ይላል ሁሉም በልቡ። ከወድያ ወዲህ እየተንጎማለሉ፣ ምን አነሥ - ምን ይጨመር - የሚሉት አስተናጋጆች ከግቢ የመጡ የተዋጣላቸው አሳላፊዎች ይመስላሉ። አስተናጋጆቹም ሆነ የምግብና መጠጥ ዝግጅት ክፍል ባለደረቦቹ ከአነጋገር እስከ አለባበሳቸው ኢትዮጵያዊነትን እያንጸባርቁ በልክ ይራመዱ ነበር።

በዚህ ዓይነት የሚስተናገደው ታዳሚ በፈገግታና በፍቅር ብቻ ሳይሆን በማስተዋልም ተሞልቷል። በዓሉ አንድነትን ብቻ ሳይሆን ሕብረት ጭምር ፈጥሯል። አንድነቱ ለወገኔ ጎዳሴን ፈንጥቆለታል። ሕብረቱ ደግሞ የማዕዱን በረከት አትረፍርፎለታል። አመሻሹ ላይ እማዶ የተቀመጡት ይህን ድንቅ ሁኔታ ሲታዘቡ የቆዩት ቅንጅቶቹ ባልና ሚስት ንግግር ለማድረግ ተነሱ። እንደ ኖህ መርከብ ሁሉን ማሰባሰብ ያስቻላቸውን እግዚአብሄርን በየተራ አመሰገኑ። የእምነት ማጽናቷን ኪዳን ከፍ ያደረገችው ቆንጅየዋ ልጃቸው አፍ በፈታችበት ፈረንጅኛ ቋንቋ ምስጋና አቀረበች። በርካታ ኢትዮጵያውያን ስለተገኙም ደስ ብሏታል። በመጨረሻ በሚጣፍጥ አፏ - "ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ" – በማለት ንግግሯን ሁሉን በሚያግባባው፣ ሁሉም በሚያዳምጠው - በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቋንቋ፣ አማርኛ ቋጨች። አይ ግብዣ - ኩርፍያ፣ ጉሽማና አግቦ፣ ሽሙጥና ስላቅ የለ። እሰጥ እገባ - ዘለፋና ግልምጫ አይታይ። መደባደብ፣ መገፈታተር፣ መናቆር፣ መናናቅ የጎሪጥ መተያየት የሌለበት የተባረከ በዓል ነበር። በዓሉ ፍቅር፣ ፈገግታ ጎዳሴና በረከትን አንግሶ አልፏል። እውን ይህ መልካም ባህርይ እሌላም ቦታ ይንጸባረቅ ይሆን?

ጓደኛዬ ለስለስ ብሎ ተመስጦ ነበር ይህን የሚያወራልኝ። "ቆንጆ ግብዣ - መልካም ጭውውት፣ ትምህርት የቀሰምክበት በዓል ነበር" አልኩት። ውሎው እኔንም አስደስቶኝ።"ታድያ ምነው ዝም አልከኝ - እንደተገናኘን፣ ክብድ እኮ ብለህኝ ነበር፣ ምን ሆነህ ነው?" ብዬ ጠየኩት።

"አይደለም፣ እጅግ ተመስጬ ነበር። ባቡሩ ውስጥ፣ በጎዞ ላይ ኋላም አንተን እስካገኘሁህ ድረስ አሰላስል ነበር - ምነው ስብሰባ ሲሆን ብዙ ሰው አይገኝም? ምነው እስኪ እንወያይ ልዩነታችንን አቻችለን በሕብረት እንቁም ሲባል የሚመጣው ጥቂት ነው? ውዝግብ፣ ንትርክ ለመስማት የሚመጣው ደግሞ ብዙ ነው። የግል ችግር ሲጋረጥበት ሁሉም ይሰባሰባል። ምንድነው ችግራችን? ምንድነው የሚያባላን? ምንድነው ባንዲራ ለይተን ሥፍራ ለውጠን ማዶ ለማዶ የሚያስቀምጠን - እያልኩኝ እያሰላሰልኩኝ ሳለሁ ድንገት ፍንጥቅ ያለልኝን

መልስ ሳወራርድ ነው አንተ ከፊቴ ድቅን ያልከው" - አለኝ።

ጓደኛዬ በእርግጥ ድንቅ ምርምር ላይ ነበር። ቅራኔው ተፈቶ፣ የዘርና የፖለቲካው ልዩነት ተወግዶ እግብዣው ላይ የታደሙት እንግዶች ፍቅር፣ ፈገግታ፣ ኅዳሴና በረከት ሲቀዱ ነበር። ከግብዣ፣ ሠርግ፣ ልደት፣ ምርቃት፣ ለቅሶና፣ ተዝካር ውጭ ይህ መልካም ነገር እንዳይሆን የሚያደረገው አባዜ ምን ይሆን?" - ስል ራሴን ጠየኩኝ እኔም በተራዬ። እንደው ለነገሩማ ብዙዎች ቅራኔያቸውን እጉያቸው ሸጉጠው፣ አለመግባባታቸውን አስወግደው፣ የፖለቲካ ልዩነታቸውን ሸሽገው እመንገድ ሲገኛኙ ትከሻ ለትከሻ ይሳሳሙስ የለ? አንዳንዶችም ከሰው እይታ ዘወር ብለው አብረው ቡና፣ ሻይ ቢራ ይጠጣሉ። ምነው ሰው ፊት የተኳረፉ ይመስላሉ? ምነው ባንድ ስብሰባ ላይ መቀመጥን ነውር አደረጉ? ከይሁዳ መሳም ይልቅ ፍቅርና እውነት አይቀድሙም ነበር?

ወገኔን ታድያ ምን አራራቀው? የፖለቲካ ልዩነት እንዳይባል የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች እግብዣው ላይ ተግባብተው ተቻችለው ይጫወቱ ነበር። የዘር ልዩነት እንዳይባል ኢትዮጵያዊ ቀለሙንና ገጽታውን እንጂ ማን ምን መሆኑን የሚያጠና አልነበረም። የሃይማኖት ልዩነት እንዳይባል ጴንጤውን፣ ኦርቶዶክሱን እስላሙን መለየት እስከማይቻል ድረስ ሕብረት ነበር። የተጣላ፣ የተኳረፈ ሁሉ ሠርግ፣ ግብዣና ተዝካር ላይ ይጨባበጣል፣ ይሳሳማል። ምነው ቁምነገሩ፣ ግንባታው፣ ትምህርቱና ውይይቱ ላይ ስሜት ይዛባል፣ ዘለፋ ይቀድማል፣ መሠረተ ቢስ ተቃውሞ ይንገደገዳል? በእርግጥ የችግራችን ምንጩ የኅብረ-ቀለማዊነቱ ጠላት ድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን የወለደው መጥፎ የፖለቲካ ባህል ነው።

ጓደኛዬ እባቡሩ ላይ እንዳለ ሲመራመር ድንገት እንደ ጮራ ፍንጥቅ ያለለት ንድፈ-ሃሳብ ይህ ነበር። "ድህነታችንና ኋላቀርነታችን የወለደው መጥፎ የፖለቲካ ባህል" - እነሆ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለታችንም በሰከነ መንፈስ መወያየትና መፍትሄ መዳሰስ ሞከርን። እስኪ ውይይታችንን አንኳር አንኳሩን እንዲህ ላስቀምጠው።

ኢትዮጵያ ድህነቱና ኋላቀርነቱ ባይንሰራፉባት ኖሮ ልጆቿን በእግዚአብሄ እቅድ እየተመራች በጣፋጭ ሕይወት የምታኖር መልካም ባህል፣ ወግና ሥርዓት የተላበሰች አገር ነበረች። ኢትዮጵያውያን ደጎች በመሆናቸው በምጣኔ ሃብት የተጎዳውን የሚረዱ ፍትህ የጎደለበትን የሚያጽናኑ፣ የሚማልዱ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚያስደስተው እግዚአብሄር የሚፈልገውን መፈጸም ሲችል ነው። መንግስተ ሰማያት ለልጁ ሠርግ ትልቅ ግብዣን በሚያዘጋጀው ንጉስ ትመሰላለች። ኢትዮጵያም ልጆቿን በአንድ ገበታ የምታስተናግድ ታላቅ የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ሃገር ነች። ኢትዮጵያ ቀድሞ የሃሴት ድምጾች እንጂ የረሃብተኞች ዋይታ የማይሰሙባት አገር ነበረች። በዓሉ እንደጉንዳን ያበረታል፣ እንደ ንብ ያደራጃል።

ደጎቹ ባልና ሚስት ያዘጋጁት የልጃቸው የእምነት ማጽናት በዓል ለእድምተኛው የባህሪ ለውጥን የሚያፋፍም፣ ኢትዮጵያዊ ጽናትን ዳግም የሚያድስ በዓል ይሆናል የሚል ተስፋ ያሳድራል። ድግሱ ላይ የተሳሳቀ ሁሉ ሽኩቻን ይረግማል። የድግሱ እንድምታ አሚታን የጎሪጥ መተያየትን ኋላ ቀርነትንም አሽቀንጥሮ በምትኩ የአላማ አንድነት ገንቢዎች ያደርጋል። በዓሉ ከመብሉና መጠጡ ባሻገር ያለውን አንድነትና ሕብረት እንዲጎለብቱ የትብብር ስነምግባር እውስጥ አዕምሯችን ውስጥ እንዲሰርጽ ግንዛቤን ይጭራል።

ድህነትና ኋላ ቀርነት እኛን ቀድመው ተደራጅተው፣ ጎራዴ ታጥቀው ዘንግ ይዘው ያስፈራሩናል። ሲያሻቸው ያጋጩናል፡ ያሻኩቱናል፣ ያቀናኑናል፣ ስም ያጠፉፉናል፣ ያገለማምጡናል፣ ያባሉናል። የበርካታ ችግራችን ምንጬ በፖለቲካ የተለወሰው የድህነቱና ኋላቀርነቱ ቅንጅት ነው።

ድህነትና ኋላቀርነት ሲቀናጁ ጠላት መላወሻ፣ መርመስመሺያ ያገኛል። ስለሆነም እንዳንደራጅ እንዳንለማ ወጥመዱን ያዘጋጃል። እጅ ሞፈር እንዳይጨብጥ ወገን ሃገሩን ሃይማኖቱን ጥሎ እንዲሰደድ ድህነትና ኋላቀርነት ተቀናጅተው ያሤሩብናል። ድህነትና ኋላቀርነት የግል ፍላጎቶችን ጉጉት በማብዛት ወይም አእምሯዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን በማሳረፍ ሚዛናዊ፣ ማህበርያዊና ምጣኔ-ኃብታዊ ዕድገትን በማመሰቃቀል ሠማያዊ አስተሳሰብን ያዛባሉ። ድህነትና ኋላቀርነት የጎዳው ግለሰብ በክፉ ሰው ምክር ይነዳል፣ ይዋዥቃል።

የድህነቱና ኋላቀርነቱን ቅንጅት የሚበጣጠሰው በነቃ አዕምሮ፣ በሥራ የደረጀ ሕዝብና የተማረ፣ ትምህርቱን

ወደ ቁሳካላዊ ኃይል መለወጥ በሚችለው ሠልጥኖ በሚያሠለጥነው ተመራማሪው ምሁር አማካኝነት ነው። ድህነቱና ኋላቀርነቱ ሲነግሡ የተማረው እንዳልተማረ ይሆናል። ተምሮ እንዳልተማረ የሆነው ምሁር ምርምርን ከማድረግ፣ ሥራን ከመፍጠር ወይም ትብብርን ከማጎልበት ይልቅ ጥላቻንና ክፍፍልን የሚጋብዙ ጋጋታዎች፣ የጓደኝነት ስብስብ ሲያሰማምር አልያም ቂምና በቀልን የሚወልዱ ትረካዎችን ሲያውጠነጥን ጊዜውን በከንቱ ይፈጃል።

በእርግጥ በአንድ ጣርያ ተሰባስቦ በአንድ ገበታ ላይ መቀመጥ የቻለ ወገን እንደምን በጋራ ፖለቲካ፣ በአንድ የሥራ ወይም የልማት ጉዳይ ላይ መሰባሰብና መወያየት አዳገተው? የጠላቶቻችን ዋነኛ ዓላማ ይህ እውን እንዳይሆን ነው። የጠላቶቻችን ዋነኛ ዓላማ ለዘመናት የተዋደቅንለት ሉዓላዊነትን የማስጠበቂ ኃይላችን እንዲዳከም ነው። ጠላቶቻችን በውዝግብ ብዛት ህብረት እንዳይደረግ መላን ይዘይዳሉ። የድህነቱ ጋሬጣ ለርኩስ መናፍስት ጥላ በመሆን ቅናትን፣ ምቀኝነትን፣ ሃሚታን፣ አግቦን፣ መናቆርን፣ ሽሙጥን፣ ዘረኝነትን፣ ልዩነትን፣ ሽኩቻን ወዘተ ያራባሉ። እነዚህ የርኩስ መናፍስቱ ውጤቶች ኋላቀርነት እንዳይወገድ ያደርጋሉ። የድህነቱና ኋላቀርነቱ ጠባሳ በእኛ በውጭ በምንኖረው ላይ እንኳን ተፅዕኖን አሳርፈው ሥልጣኔን፣ መቻቻልን ሕብረትን ምስጢር አድርገውብናል።

እግዚአብሄርን መውደድ ወገንን ከመውደድ ጋር ይያያዛል። ወገንን መውደድ ከሥራ ጋር ይያያዛል። ሥራ መውደድ ድህነትን ይቀርፋል። ሥራ መውደድ ኋላቀርነትን ያከስማል። ሥራ ለደሞዛዝ ብቻ ሳይሆን ሃገርን ለማበልጸግ የሚያስችለውንን ባህርይን ለማነጽ ይጠቅማል። እግዚአብሄር ሁልጊዜ ይሰራል፣ አያንቀላፋም። ይህ እኛም ልንወርሰው የሚገባን ትልቁ ሥነ-ምግባር ነው። ሥራችን ሲቀናጅ ድህነቱን ያጠፋል። አንድነታችን ሲጠናከር ጠላቶቻችን መላወሻ ያጣሉ። ህብረታችን ሲቀናጅ ደግሞ ኋላቀርነታችን ከስሞ የአምላክ በረከት ይትረፈረፋል።

አሁንም ገና ሥራ አለን። እንደቀድሞ አባቶቻችን የሃገር ጉዳይን ማስቀደም ይኖርብናል። አንድነታችን እንዲጠነክር ጊዜና ሥፍራ ሳይወስነን የትም ቢሆን ፍቅራችንን ማብዛት ጥላቻን መቀነስ ይኖርብናል። ጥላቻ እልህን ታባብሳለች። ኢትዮጵያ ግብር እያበላች ልታሰባስበን አቅሟ ገና አልበረታም። አቅሟ ዳግም እንዲበረታ ማገር፣ አውታር፣ ምሰሶና ዋልታ የመሆን ግዴታ አለብን። አውታር እንዳንሆን፣ ማገር እንዳንሆን፣ ምሰሶ እንዳንሆን፣ ዋልታ እንዳንሆን የሚስቡንን፣ የሚያዘናጉንን፣ የሚያዋዥቁንን፣ የሚያናቁሩንን ወጊዱ እንበላቸው። እነሆ ኢትዮጵያ ሁላችንንም በእቅፏ አድርጋ በአንድ ገበታ በአንድ ማዕድ አስቀምጣ ከወንዞቿ እያጠጣች፣ ከፍሬዎቿ እያቋደሰች ልጆቿን የምታሰባስብበት ቀን ሩቅ አይደለም።

እኔና ጓደኛዬ እንዲህ እንዲህ እያልን ስንወያይ ቆይተን ሁለተኛ ቢራችንን ጨርሰን ሳይመሽብን ተለያየን። እንደው ልማድ አድርገን ቡናም፣ ለስላሳም ሆነ ቢራ ስንይዝ ሃገራዊ ጉዳዮችን እያነሳን እንወያያለን። የሰው ስም እንዳናነሳ፣ የሚሰሩትን እንዳንተች ስደትን እንዳናሟሙቅ ተማምለናል። በሁለታችን ማህከል አስመሳይነትና ግብዝነት ቦታ እንዳይዙ ጥንቃቄ እናደርጋለን። ስንለያይ በተወያየነው ላይ መቋጫ መንደፍን አንረሳም። በእርግጥ ይህ ሁሉ ካለ እግዚአብሄር ድጋፍ አይሆንም።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ፣ ድህነትንና ኋላቀርነትን እንድናስወግድ ማስተዋል ያብዛልን። አሜን

ይድነቅ